

ቅጽ 3፣ ችግር 4

# የAccess ተሳፋሪዎችንደህንነት እና ምቾትን የሚያሻሽሉ ጥቂት ጠቃሚ ዝማኔዎች/ማሻሻያዎች እዚህ አሉ።

## የተሳፋሪዎች Rider's Choice ፕሮግራም ማሻሻያዎች




የኪንግ ካውንቲ Metro እና MV Transportation ለAccess ፓራትራንዚት አገልግሎት ጉዞዎችዎ በሰዓቱ የመገኘትን አስፈላጊነት ይገነዘባሉ። ጉዞው ለህክምና ቀጠሮም ይሁን ለማህበራዊ መውጫ፣ እኛ አለንልዎት።

Access የጋራ ጉዞ ስርዓት ስለሆነ—ሌሎች ተሳፋሪዎች ከእርስዎ ጋር ሆነው—ወደ መድረሻዎ በጊዜ መድረስ አስፈላጊ መሆኑን እንገነዘባለን። ወቅታዊ ፖሊሲዎችን እና ሂደቶችን በጥንቃቄ ከገመገምን እና ከAccess ፓራትራንዚት አማካሪ ኮሚቴ (Access Paratransit Advisory Committee, APAC) ጋር ከተቀናጀን በኋላ Access የRider's Choice ፕሮግራምን ለተሳፋሪዎቻችን የበለጠ ተለዋዋጭ እና ለተጠቃሚ ምቹ እያደረገ ነው።

ካለፈው ዲሴምበር ጀምሮ፣ የRider's Choice ተሳፋሪዎች የ30 ደቂቃ የመውረጃ ጊዜያቸው ገደብ ከመድረሱ በፊት በመድረሻቸው ቦታ ሊወርዱ የሚችሉበትን አማራጭ ሰጥቷል::።

ወደዚህ ጃንዋሪ 2024 ስንመጣ፣ የበለጠ ምቹ ለማድረግ እና ለደንበኞቻችን በጉዟቸው ላይ የበለጠ ቁጥጥር እንዲኖራቸው ለማድረግ የRider's Choice እናሻሽላለን፦

- ጉዞዎ ከተጠበቀው ጊዜ ቀደም ብሎ ወደ ቀጠሮው ይደርሳል ብለን ከገመትን እና በAccess ቫን ላይ ከተሳፈሩ፣ የስልክ ጥሪ ሊደርስዎ ይችላል (የጽሑፍ መልእክቶች በቅርቡ ይጀመራሉ!)።
- በዚያ ጥሪ ላይ ኦርጅናሉን የመውረጃ መስኮቱን (የጊዜ ገደቡን) የማቆየት ወይም ቀደም ብሎ መውረድን የመምረጥ ምርጫ ይሰጥዎታል። እንዲሁም ለማንኛውም ጥያቄዎች በቀጥታ ወደ ወደሚያስማራው ክፍል (ስምሪት) ሊተላለፉ ይችላሉ።
  ጥሪ ካልደረሰዎት ወይም ዋናውን የመውረጃ ጊዜ ካልመረጡ አሁንም ተሽከርካሪውን የመጠበቅ ወይም ቶሎ የመሄድ ምርጫ ይኖርዎታል—በሚወርዱበት ጊዜ ከአሽከርካሪዎ ጋር ይህንን ይነጋገሩ።

በእነዚህ ማሻሻያዎች  ምርጫዎትን ለማድረግ አራት የተለያዩ መንገዶች ይኖሩዎታል፡-

- በምዝገባዎ ወይም በግል የጉዞ ቦታ ማስያዝ፣ የቦታ ማስያዝ ቡድኑን እንዲያውቅ ያድርጉ።
- ጉዞዎ ከመጀመሩ በፊት በማንኛውም ጊዜ፣ የሚያስማራውን ክፍል (ስምሪትን) ለማነጋገር ይጠይቁ።
- በጉዞዎ ወቅት፣ አዎቶማቲካሊ ለሚደርስዎት የስልክ ጥሪ ወይም የጽሁፍ መልዕክት ምላሽ ይስጡ።
- በመውረጃ ሰዓት፣ አሽከርካሪዎን ያሳውቁ።

እባክዎ በ206-553-3000 ለደንበኛ አገልግሎት ቡድናችን የRider's Choiceልምድዎን ማካፈልዎን ያረጋግጡ።

## ወደ 2024 ስንገባ Access ያለበት ሁኔታ
## በGwen Clemens፣ የኮንትራት አገልግሎት ማኔጂንግ ዳይሬክተር

ወደ 2024 ስንገባ ራሳችንን ለለውጦች እናዘጋጃለን፤ አዲሱን ዓመት ለመጀመር እና ከቤተሰብ እና ከጓደኞች ጋር ጊዜ ለማሳለፍ በጉጉት ስንጠባበቅ ለቀኖች እና ለአየር ለውጥ እንዘጋጃለን— እነዚህ አንድ ላይ የሚያያይዙን እና የተሻለ እንድንሰራ የሚያነሳሱን  ነገሮች ናቸው።

የAccess አስተማማኝነትን እና የጉዞ ተሞክሮዎን ለማሻሻል በምንሰራበት ጊዜ ላሳዩት ትዕግስትምስጋናዬን መግለጽ እፈልጋለሁ። በዚህ አመት ያሳካናቸውን አንዳንድ ቁልፍ ግቦችን ልናካፍላችሁ እና በ2024 ሁላችንም በጉጉት የምንጠብቃቸውን ነገሮች በአጭሩ ልንነግርዎ እንፈልጋለን!



Gwen Clemens

በ2023 የነበሩ ቁልፍ ስኬቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- አሁን ያለውን የAccess ውል ለ2 ዓመት ለማራዘም  መደራደር። ይህ ማራዘሚያ የቁልፍ አፈጻጸም አመልካች (Key Performance Indicator, KPI) ማበረታቻዎችን እና ፀረ-ማበረታቻዎችን ወደነበረበት ለመመለስ ወሳኝ ነበር። የKPI ማበረታቻዎች እና ፀረ-ማበረታቻዎች የMetro የአፈጻጸም ደረጃዎችን የማስፈጸም እና የእኛ ተቋራጭ MV Transportation ከውል በላይ እና የደንበኞች አገልግሎት ዝቅተኛ ስራዎችን እንዲያከናውን የማበረታቻ ቀዳሚ መንገድ ነው።

- ለደመወዝ፣ ለጥቅማጥቅሞች፣ ለነዳጅ እና ለተሽከርካሪ ክፍሎች እንደ Solid Ground ባሉ በMV Transportation እና ኢጋሮቻቸው ላይ ለተጨመሩ ወጪዎች ምላሽ መስጠት።
- ተለዋዋጭ የጉዞ ፍላጎቶችን ለማንፀባረቅ የዋጋ አወጣጥ መዋቅራችንን ማዘመን። ውሉ በዋነኛነት በገቢ ሰአታት ላይ የተመሰረተ ሲሆን እነዚህም በጉዞ ፍላጎቶች የሚመሩ ናቸው። የእኛ የአሽከርካሪነት ደረጃዎች በአሁኑ ጊዜ ከ2019 የአሽከርካሪነት ደረጃዎች 69% ላይ ናቸው።
- በአዲሱ የAccess የደንበኛ ብቁነት (Access Customer Eligibility, ACE) የቴክኖሎጂ ማሻሻያ ፕሮጀክት ላይ ሥራ መጀመር። ይህ ፕሮጀክት የAccess ትራንስፖርት አገልግሎቶችን የማመልከቻ ሂደትን ያዘምናል።
- ለተመሳሳይ ቀን አገልግሎት ሙከራ ማቀድ። ይህ ተነሳሽነት Access ተሳፋሪዎች ለጉዞዎች የአንድ ቀን አገልግሎት እንዲኖራቸው ያስችላቸዋል። አንድ ኮንትራክተር፣ VIA፣ ለዚህ የሙከራ ፕሮጀክት ኃላፊ ይሆናል። በ2024 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማየት መጠበቅ ይችላሉ።
- የአሜሪካ የአካል ጉዳተኞች ህግ (Americans with Disabilities Act, ADA) የፌዴራል ትራንዚት አስተዳደር (Federal Transit Administration, FTA) የሶስት አመት ኦዲት እና ግምገማ ከSound Transit ጋር በማስተባበር። ለAccess ትራንስፖርት የADA ጉድለቶች ግኝቶች አልነበሩም።
- በCOVID ወረርሽኙ ወቅት የተቀመጡ አንዳንድ ለውጦችን ማስተካከል።

**በ2024 የሚፈለጉ ቁልፍ ፕሮጀክቶች**

- የተመሳሳይ ቀን አገልግሎት ሙከራ ሙሉ ትግበራ።
- የAccess ጉዞ የዳሰሳ ጥናት ስርጭት። ይህ የዳሰሳ ጥናት አገልግሎቱን እንዴት እየተሰጠ እንዳለ አስፈላጊውን ግንዛቤ ይሰጠናል።
- የAccess' የመጀመሪያ 100% የኤሌትሪክ ፓራትራንዚት ተሽከርካሪዎችን ማሰማራት። ይህ የሙከራ ፕሮጀክት Metro ተግባራዊ እና የደንበኞችን ተፅእኖ የበለጠ ለመረዳት እንዲረዳው በአገልግሎት ላይ የሚሰማሩ አራት ሙሉ በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ፓራትራንዚት ተሽከርካሪዎችን ይመለከታል።
- ደንበኞች  Rider's Choice ን የሚመርጡባቸው አዳዲስ መንገዶች (በመጀመሪያው ገጽ ላይ የ*Rider's Choice ፕሮግራም ማሻሻያዎችን* ይመልከቱ)።
- ልዩ የመጓጓዣ ፍላጎት ላላቸው ግለሰቦች አዲስ የ**FindARide.org** ክልላዊ የጉዞ ዕቅድ አውጪ ማሰማራት—ይህ ሥራ ከኪንግ ካውንቲ Metro ጋር በመተባበር በHopelink የሚመራ ነው።

Access Transportation

## APACን በመቀላቀል Accessን ወደፊት መምራት!

የኪንግ ካውንቲ Metro Access ፓራትራንዚት አማካሪ ኮሚቴ (APAC) ለMetro፣ የኪንግ ካውንቲ ስራ አስፈፃሚ እና የኪንግ ካውንቲ ምክር ቤት በመጓጓዣ ጉዳዮች እና ፖሊሲ ላይ ለአካል ጉዳተኞች የህዝብ ማመላለሻ አገልግሎትን በእኩልነት ማቅረብን በተመለከተ ይመክራል። APAC በካውንቲው ባሉ መላው አባላት ማለትም የAccess ተሳፋሪዎች: የAccess ተሳፋሪዎች ቤተሰብ አባላት፣ ለAccess ተሳፋሪዎች አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች ተወካዮች እና እንግሊዝኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚናገሩ Accessተሳፋሪዎችን በሚደግፉ ድርጅቶች ተወካዮች የተዋቀረ/የተመሰረተ ነው።

በ2023፣ APAC የAccess ተሽከርካሪዎችን በሰዓቱ የሚደረግ አፈጻጸም ለማሻሻል የሚረዳውን እና የማህበረሰቡን ተደራሽነት እና ማህበረሰባችን የMetro ADA የሽግግር እቅድ ተሳትፎን እንዲያገኝ ለማስፋት የሚረዳውን መመሪያ ለMetro ሰጥቷል። በተጨማሪም APAC በፈጠራ አዲስ ተመሳሳይ ቀን አገልግሎት ላይ ምክር ሰጥቷል እና ለሁሉም ተሳፋሪዎች Access መጓጓዣን እንዴት ማሻሻል እንደሚቻል ለMetro ሰራተኞች ቀጣይነት ያለው አጠቃላይ አስተያየት ሰጥቷል።

**APACአዳዲስ አባላትን በንቃት እየመለመለ ነው።** በሚከተሉት የኪንግ ካውንቲ ካውንስል ዲስትሪክቶች የሚኖሩ ከሆነ፣ የAccess ተሳፋሪ ከሆኑ ወይም ከላይ የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች የሚያሟሉ ከሆነ እና የእርስዎን እውቀት፣ የማህበረሰብ ግንኙነት፣ ዳራ እና ልምድ ማካፈል ከፈለጉ እባክዎ ያመልክቱ። ለነዚህ የምክር ቤት ወረዳዎች ክፍት ምልመላ እየተካሄደ ነው:-

- የኪንግ ካውንቲ ምክር ቤት ዲስትሪክት 2
  - Renton፣ Tukwila፣ የአኒንኮሮፖሬትድ ኪንግ ካውንቲ እና ማዕከላዊ/ደቡብ Seattle ክፍሎችን ያካትታል።
- የኪንግ ካውንቲ ካውንስል ዲስትሪክት 3
  - Bothell፣ Carnation፣ Duvall፣ Issaquah፣ North Bend፣ Redmond፣ Sammamish፣ Skykomish፣ Snoqualmie፣ Woodinville እና ሰሜን ምስራቅ የአኒንኮሮፖሬትድ ኪንግ ካውንቲን ያካትታል።
- የኪንግ ካውንቲ ካውንስል ዲስትሪክት 6
  - Beaux Art Village፣ Bellevue፣ Clyde Hill፣ Hunts Point፣ Kirkland፣ Medina፣ Mercer Island፣ Redmond፣ Yarrow Point እና የአኒንኮሮፖሬትድ ኪንግ ካውንቲ ክፍሎችን ያካትታል።

ማመልከቻዎች እስከ ፌብሩዋሪ 11፣ 2024 ድረስ ክፍት ይሆናሉ። እንዴት ማመልከት እንዳለብዎት  የበለጠ ለማወቅ **kingcounty.gov/metro/APAC**ን ይጎብኙ።